## አቅምግንባታ ሴክተር እቅድ

የተጀመረው ፈጣን ልማት ቀታይነት ኖሮት ከልማቱ ህዝቡ በላቀ ደረጃ ተተቃሚ እንዲሆን ለማድረግ መልካም አስተዳደር ሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውት ትግበራን በየደረጃው እውን በማድረግ በመልካም አስተዳደር እምርታ ማምጣት የሚያስችል አቅም ግንባታ ሴክተር እቅድ በዚህ በጀት አመት በትኩረት ሚፈጸም ሲሆን መንግስት ተቋማትአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋናውጤታማ በማድረግ መንግስት የልማት ፖሊሲዎች ፕሮግራሞችና እስትራቴጂዎች ተግባራዊ ማድረግ የሚስችል ተቋማዊ ለውት ማረጋገጥ  ልተማከለ አስተዳደር ጥያቄዎች የሚፈቱበትን ስልት መቄስ ስልጠና በመስጠትና ብቃት ለው የሰው ሃል በማፍራት የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም መገንባትና መረጃዎችን በማሰባሰብ በማደራጀት በመተንተን ለተለያዩ መረጃ ፈላጊዎች ማሰራጨት የበጀት አመቱ ቁልፍ ስራዎች ሆናሉ፡፡

በመሆኑም የሴክተሩ ዝርዝር እቅድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-
መሰረታዊ ስራ ሂደት ለውት ትግበራ በተሟላ ሁኔታ በሁሉም ደረጃና በሁሉም መንግስታዊ ተቋማት እንዲፈፀም ተጠንተው የሚወርዱ የጥናት ውጤቶችከሆኑ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው እንዲፈፀሙ የሚደረግ ሲሆን ከBPR ጋር የተጣጣመየስራ ምዘናና ደረጃ አሰጣጥ ስርአትና ውጤት ላ የተመሰረተየማትጊያስርአት ስራላይ እንዲውል ይደረጋል ለስኬቱም ብቃት ያለው ክትትልና ድጋፍ ይሰጣል፡፡በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውት ጥናት መሰረት ምደባ ያላገኙሰራተኞችመንግስት ባስቀመጠላቸው ሌሎች አማራጮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስፈላጊው ሁኔታ ይመቻቻል፡፡
በበጀት አመቱ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ሚዛናዊ የውጤትተኮር እቅድ/BSC/ ስርአት የሚዘረጋ ሲሆን በአፈፃፀሙ ላይ አመራሮችና ሰራተኞች ስልጠና እንዲወስዱ ደረጋል፡፡በየደረጃው ባሉ የመንግስ ተቋማት ቀልጣፋ የኣገልግሎት አሰጣጥና ቅሬታ ማስተናገጃ ስርአት በጥብቅ እንዲፈጸማ ይደረጋል፡፡
በሁሉምወረዳና ቀበሌ መልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግበራዊ ለማድረግ አዲሱን ኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አደረጃጀትና አሰራር ስራላይ የሚውል ሲሆን በሁሉም ቀበሌ የኢንስፔክሽንቡድን የማቋቋምና በኢንስፔክሽን ሱፐርቪዥን መመሪያ ላይ አስፈጻሚ አካላትስልጠና ይሰጣል፡፡
በተሌ የአርብቶ አደር አካባቢ መልካም አስተዳደር ፓኬጅለመጀመሪያ ጊዜበስራላይ የሚውል ሲሆን በፓኬጁ ዙሪያ በአመራሩና አስፈጻሚው ዘንድ ግንዛቤ መፍጠር ተግባራት ይከናወናሉ፡
፡
በሌላ መልኩ በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ መሰረት ከሚመለከታቸው ሴክተርመ/ቤቶች ጋር በመተባበር ብቃት ባለው መስፈርት ሞዴል አርሶአደሮችን መንደርና ቀበሌዎችን መለየትና ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር የማስፋት ስራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡
በሁሉም ቀበሌ ስራ አስኪያጆች በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰሩ አሰራርና አደረጃጀት ስርአት ሚዘረጋ ሲሆን የገጠር ልማት ተግባሮች በቀበሌ ደረጃ ተጣምሮና ተቀናጅተው እንዲፈፀሙ ደረጋል፡፡ በቀበሌደረጃ የቅሬታ ማስተናገጃ ስርአትን መረጃና ጉዳይ አቀባበል አሰራር እንዲጠናከር ደረጋል ፡፡
ፍትህ ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራምን በተመለከተ የፍትህ ተቋማትን አገልግሎት አሰጣት

ቅልጣፌና ውጤታማነት ለማረጋገጥ በየደረጃው የተቋቋሙ  የፍትህ ስርአት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ የሚደረግ ሲሆን በሁሉም የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች የኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር ስምምነት በመፈጸም ስርአቱ ወደመሬት እንዲወርድ ይደረጋል ፡፡መሰረታዊ የስራሂደት ለውጥ ትግበራን ተከትሎ እጅከፍንጅ ለተያዙ ወንጀለኞች የእለትፍርድ ውሳኔ አሰጣጥ ስርአት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡በዲሞክራሲስርአት ግንባታ ትልቁን ሚና የሚጫወቱት የህዝብ ምክርቤቶች እንዲጠናከሩ ተገቢው ድጋፍ ይሰጣል፡፡

በኢንፎርሜሽን ኮሙኑኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት አቅርቦትና ስርጭት ዘርፍ በሁሉም ሴክተሮች መሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ትግበራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ጥረት የሚደረግ ሲሆን የኢንፎርሜሽን ኮሙኑኬሽንቴክኖሎጂ መሰረተልማት የማስፋፋት በዘርፉ ሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት ተበላሹ የ ኣይሲቲ መሳሪያዎችን የመጠገንና የ ኢኮቴ መዋቅርን እስከወረዳ የማጠናከር የማህበረሰብ መረጃ ማእከልን ብቃት ያለውን አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻልና በሁለት ወረዳዎች የወረዳኔት
መሳሪያተከላ ማስፈጸም በትኩረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

ለተግባሮቻችን ሁሉ ስኬት ማስፈፀም አቅም ቁልፍ መሆን ይታወቃል፡፡በዚሁ መሰረት በአጭርና በለዥም የስልጠና ፕሮግራሞች አመራርና ሰራተኛ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሚደረግ ሲሆንበዚህ ሂደት በመጀመሪያ ዲግሪ 30 በሁለተኛ ዲግሪ 20 ስራላይ ካሉት ሰራተኞች በለውት ፕሮግራሞች በፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላ ስልጠና እንዲያገኙይደረጋል፡፡

በሰው ሃይል ስራ አመራር ዘርፍ የሰራተኛ ስምሪት አስተዳደርና ጥቅማ ጥቅምን አስመልክቶ የሚወጡ ደንቦች መመሪያዎች ህጎች እንዲሰራጩ በአግባቡ ስራላይ እንዲውሉ የሚደረግሲሆን በመምሪያዎቹና ህጎቹ ላይ ግንዛቤ የመፍጠርና የአፈፃፀም ትትል የማድረግ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

በበጀት አመቱ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመንግስት ሰራተኞች መረጃ የሚደራጅሲሆን ሌሎች ወቅታዊ መረጃዎችን የማሰባሰብ የመተንተንና ለተጠቃሚ የማሰራጨት ስራ ይሰራል፡፡ በሌላ መልኩ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳዊ ጥናት እንዲሁም የተገልጋዮች እርካታ ደረጃ መለኪያ ጥናት የሚካሄድበት ሲሆን የሴክተሩ የ5 አመት ስትራቴጂክ እቅድም እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

የስርአተ ፆታና ኤችአይቪ ኤድስ መከላከል ተግባርን በተመለከተ የአርብቶ አደር አካባቢ ሴት ተማሪዎችን የማበረታታት ሴቶች ለስልጣን ከመብቃታቸው አኳያ ፓናል ውይይት የማዘጋጀት ስራ የሚሰራ ሲሆን በኤችአይቪ ኤድስ የተጎዱ ወገኖችን ለመደገፍ ሰራተኛው የሚያዋጣውን መዋጮ ከማጠናከርባሻገር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራሉ፡፡